# በገሃነም እሳት መሐል የሚገኝ መንግስተ ሰማያት!

ከበልጅግ ዐሊ

አንድ ጎረቤቴ የሆነ ግለሰብ አዲስ አበባ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ ስለ ሀገራችን ሁኔታ ሊጫውተኝ እስካለሁበት ድረስ መጣ። “ስማ አትሞኝ“ ብሎ ጀመረ። “ሂድና ቤተሰቦችህን ጠይቅ፣ ትንሽም ቤት ነገር ቀልስ፣ ጊዜ ደርሶ አገርህ ስትመለስ ማረፍያህ ይሆንሃል። ወንድሜ ሆይ ልምከርህ ፖለቲካው እንደሆነ አንዴ የማይስተካከል ሆኑዋል። እኔ ምን ያህል እሳተፍ እንደነበር ታውቃለህ።ሀገር ቤት ደርሼ ከመጣሁ በኋላ ግን ተለውጫለሁ“።

“ከፖለቲካው ምንም ትርፍ አታገኝበትም።እንደምታየው የዘመኑ ፖለቲካ ባለ ሁለት ስለት ቢላዋ ነው። በአንደኛው የግል ጥቅምህን ስትቆርጥበት በሁለተኛው ደግሞ የግል ጥቅምን የማይከለክል የሰለጠነን ፖለቲካን ማኪያሄድ አስፈላጊ ነው። ቀልጣፋ ሁን።እንደሌሎቹ በሙሉ ግዜህ እራስህ ለመጥቀም አትቦዝን“።እራስን ለመጥቀም ተጣጣር እያለ ምክሩን ሲንጎደጉድ በጣም ተገርሜ በፅሞና ማዳመጤን ቀጠልኩ።እሱም በሰፊው ምክሩን ቀጠለ።

“መቼም አዲስ አበባን አሁን ብታየው አታውቀውም።የድሮው አዲስ አበባ አይመስልህም። የቡና ቤቶቹ ብዛትና ጥራት ጉድ ነው። እዚህ አውሮፓ ካሉት የሚተናነሱ አይደሉም። የሃገሩ ሕዝብ ሁሉ ሚሊዮኔር ሆኑዋል ወይ ብለህ ነው የምታስበው። ይጠጣል፣ ይጨፈራል።የዘንድሮውን የሴቶቹን ቁንጅና ልነግርህ አልችልም።እምዬ ማርያምን ነው የሚመሳስሉት። ጠቅላላው ህዝብ ደስተኛ ነው።ገበሬዎቹ ሳይቀሩ ሃብታሞች ሆነዋል። ወደ አቃቂ አካባቢ ያሉ ገበሬዎች መሬት እስከ ሚሊዮን ድረስ ይሸጣሉ።አዲስ አበባ ውስጥ በአንዲት ቀን አዳር ሚሊየኔር መሆን ይቻላል። ዋናው እንዴት ቱጃር መሆን እንደሚቻል ማወቅ ነው።ብነግርህ አታምነኝም ወንድሜ! የመኪናው ብዛትና ጥራት ጉድ ነው የምትለው። ቶዮታውንና ሌላውን መኪና ተወውና ሃመሩንና ሜርሴዲሱን መቁጠር እስከሚሰለችህ ሃገሪቱን አጥለቅልቀውታል“።

„ለመዝናናት ከፈለግህ ደግሞ ሲሻ ቤት አለልህ ።መደነቅ ብቻ ነው። ምን የመሰለ ቪላ ውስጥ ሲሻህን እያጨስክ ጫትህን እየቃምክ መዋል ትችላለህ። ምን ምን የመሳሰሉ ሴቶች አብረውህ ይቅማሉ፣ ያመሻሉ፣ከፈለግህ አብረውህም ያድራሉ።ሲሻ ማጨሻው ቤት ውስጥ ነው ቢዝነስ የሚሰራው።የብዙ ሃብታሞች ገንዘብ የሠሩበትን ገድልን እዛው ትሰማዋለሁ።አየር ባየር ነግደው ሰማይ የደረሱ ስንት እንዳሉ ትረዳዋለህ።አብረሃቸው ከዋልክ የቢዝነሱን የተደበቀ ሚስጥር ወለል ብሎ እንዲታይህ ያደርጋሉ።እዚሁ ሲሻ ቤት ውስጥ የጉምሩኩን ቁልፍ ሰዎች፣የክልሉን ሃላፊዎች፣የፖለቲካውን ተንታኞች፣ የወያኔ ባለስልጣኖችን መተዋወቅ የምትችለው።ቀስ በቀስ ትግባባቸውና በምትፈልገው የቢዝነስ ዓይነት ይረዱሃል“።

“አዳዲስ ስለሚሰሩት ቤቶቹ እንዴት ማስረዳት እንደምችል አላውቅም።የተሰሩትን ቪላዎች ብትመለከት አታምንም። በሶስተኛ አለም ሀገር እንደዚህ አይነት የተሟሉ ቤቶች ይኖራሉ? ብለህ መደነቅህ አይቀርም።መቼም አንተ መከራከር ትወዳለህ ብዬ ምን እንዳደረኩ ታውቃለህ? ፎቶ አንስቼልህ ነው የመጣሁት“።ተመልከተው ብሎ ፍቶውን አሳየኝ። አንስቶ የመጣውን ፎቶ ልብ ብዬ ተመለከትኩት። በትልቅ አጥር የተከበበ ግቢ ነው።በአጥሩ ውስጥ ያለው ቤት ግን አይታይም።

የምታሳየኝ ፎቶ እኮ አጥር ብቻ ነው ቤቱ አይታይም ለመሆኑ ቤቱ የት ነው ያለው ? አልኩና ጠየቅሁት።

“አጥሩ ውስጥ ነዋ!! “ ብሎ በእኔ አላውቂነት በጣም ሳቀ።ምን እንዳሳቀው ባይገባኝም አብሬው ሳቅሁ። እሱ በእኔ መሃይምነት እኔ ደግሞ በእሱ ደንቆሮነት አብረን ሳቅን።

እኔም ቀጥዬ እንዲህ ብዬ ጠየቅሁት።እንኳን እኔ አንተም ቤቱን አላየኸውም።እንዴት ልታደንቀው ቻልክ አልኩት?

“የቤቱን ጠባቂ ዘበኛ ለምንኩትና ገብቼ ውስጡን አየሁት። ግን ፎቶ እንዳላነሳ ዘበኛው ከለከለኝ።ታውቃለህ ዘበኛው በፊት ምን ይሰራ እንደነበር። የቀድሞ የአየር ወለድ ሻለቃ ነበር። በኤርትራ ጦርነት ትልቅ ጀብዱ የሰራ መሆኑን ነገረኝ። አሁን ዕጣ ክፍሉ ሆኖ ዘበኝነት እንደተቀጠረና ቤተሰቦቹን እንደሚያስተዳድር አጫወተኝ“።

አጥሩ ግን እንደ ጥንት የአውሮፓ ከተማዎች ጠላት ለመከላከል የተሰራ ይመስላል።ብዬ የሚያሳዝነውን የሻለቃ ታሪክ ቀየርኩት።

„አዎ አንዳንድ አስቸጋሪዎች አይጠፉም አለኝ።በዚህ ምክንያት አጥሩ ቢተልቅ አትገረም።በአካባቢውም ካለው ቆሻሻ ለመለየት አጥሩ አስፈላጊ ነው።ቤቱን ከውስጥ ብትመለከት አታምንም።ከማዋኛ ስፍራ እስከ ሳውና አለው። ውስጡ መንግስተ ሰማያትን ይመስላል።ከቤቱ ውጭ ያለውን አካባቢ ለተመለከተ በዚያ በቆሻሻ ስፍራ እንደዚህ ዓይነት መንግስተ ሰማያት ይኖራል ብሎ ለመገመት ያዳግታል“።

ታዲያ ይህ ትልቁ ግንብ መንግስተ ሰማያትን ከገሃነብ ለመለየት ነው?ብዬ የማሾፍ ፈገግታ አሳየሁት።

“ተወኝ እባክህ! ይህ አባባልህ የድሮ የኮሚኒስቶች መፈክር ነው። እኔ አሁን ልመክርህ ነው የመጣሁት።ሃገሪትዎ እንደ ድሮ እንዳትመስልህ። አሁን መፈክሩ ተቀይሮል። መሬት ላራሹ ብለህ ብትጨፍር ማንም አይሰማህም። አሁን ማለት ያለብህ መሬት ለእራሴ ነው። ደግሞ አጥር ለቤት አይስፈልግም እንዳትለኝ።ወንጀል እንኳን በኛ ሀገር በስለጠነው ሃገር ስላለ ስለ አጥሩ ባንነጋገር ይሻላል“።

ለችግረኛው ሕዝብ መቆም ያለፈበት መፈክር ነው የምትለው?ብዬ ጠየቅሁት።

“ጭቁኑን ሕዝብ እንኳ እኛ እነ ሌኒንም ነጻ አላወጡትም።የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ እንደግፋለን ሲሉ ምን ማለታቸው ይመስልሃል? ነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ማለት ሃብታምና ደሀን መፍጠር እኮ ነው። የመደብ ክፍፍል ያለበትን ሥርዓትን መገንባት ነው። ለተጨቆነ ሕዝብ መታገል የምትለው ደግሞ ፋሽኑ እንደ አፍሮና እንደ ሻፍት ጫማ ያለፈበት ነው“።አለኝ

አሁን አንተ የምትለኝ ሀገሪቱ አድጋለች ነው? አልኩና ሌላ አጀንዳ ቀየርኩ።

“በጣም እንጂ“። ብሎ በመኩራራት መለሰልኝ።

በቡና ቤቶችና በሲሻ ቤቶች ብዛት? ብዬ መልሱን መጠበቅ ጀመርኩ።

“እሱስ ቢሆን እድገት አደለም እንዴ ? ከውጭ የሚመጡ ኢንቬስተሮች መጀመሪያ የሚዝናኑበት ሆቴሎችና ክለቦች ያስፈልጓቸዋል“።

ምን ማለትህ ነው መብራትና ውሃ በፈረቃ እያታደለ፣በሚሊዮን የሚቆጠር እየተራበ ነው ሀገር አደገች የምትለው?ብዬ ጠየቅሁት።

“እንደመሰለኝ አንተ አሁንም የሃገር እድገትን የምትለካው በድሮው በኮምኒዝም ግዜ እንደነበርው የምርት ግንኙነት፣ የምርት ሃይሎች፣የማምረቻ መሳሪያዎች፣የፋብሪካ ብዛት፣ የገበሬው ማዳበሪያ ማግኘት፣ የሥራ አጥ ቁጥር በሚለው መለኪያ ነው።አሁን ዘመኑ ተቀይሮአል። የሃገሪቱ እድገት የሚለካው በሃብታሞች ቁጥር ነው። ስንት ሚሊዮኔር አለ በሃገሪቱ ነው ጨዋታው። ያ ነው ደግሞ በምዕራብያውያንም ተቀባይነት ያለው።የአለም ባንክም የሚመለከተው ይህንኑ ነው“።

የሀገሪቱን እድገት እንተወውና ስለቤቶቹ አሰራር ንገረኝ አልኩት።

“ስለ እሱ ከፈለግህ በደንብ አስረዳሃለው“።አለኝ ደረቱን ነፍቶ በአዲስ አባባ ዕውቀቱ በመኩራራት። “አንዳንድ ሰፈሮች ከከተማው እድገት ጋር አልሄዱም በማለት መንግሥት ይፍረሱ እያለ ነው። ድሃዎችን በከተማው መሃል ማስቀመጥ የኢኮኖሚው ዋልታ የሆኑትን ኢንቬስተሮች ማሳቀቅ መሆኑንና የከተማውን እድገት መገደብ መሆኑን ታምኖበታል።በዚህም ምክንያት በከተማው ውስጥ ያሉ አሮጌ ቤቶች ፈርሰው አዲስ እንዲሠሩ ታዞአል። በአሮጌው ቤቶች ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ኑዋሪዎች ለቦታቸው ግምት እየተሰጣቸው ከከተማ ውጭ ባሉ ቦታዎች ላይ እንዲሰፍሩ ይደረጋል። የቀድሞው ነዋሪዎች መንግስት በእነዚህ ቦታው የሚፈቅዳቸውን ቤቶች መስራት አይችሉም እንጂ ቅድሚያ እንዲሰሩ ለእነርሱ ይሰጣቸዋል“።

ኑዋሪዎቹ የታ ይሄዳሉ ታዲያ?ብዬ ጠየቅሁት።

“እነርሱማ ወደ ተዘጋጀላቸው የማረፊያ ቦታ ይሰፍራሉ“።

ከመኖሪያቸው ወጥተው ስደት ሀገራቸው ውስጥ ይጀምራሉ ማለትህ ነው?

“እንደሱ አደለም። ለምሳሌ በቅርቡ በተክለ  ሃይማኖትና  በልደታ አካባቢ ያሉት አነስተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች የሚኖሩበትን ቤቶች ፈርሰው ቦታው ለሃብታሞች ተስጥቶ ለቦታው ተመጣጣኝ የሆነ ሕንፃ ሊገነቡ  ነው።እዛ ቦታ ላይ የሚኖሩት ደግሞ ይህንን ቦታ ለቀው ከአዲስ አባባ ውጭ ቦታ ይሰጣቸውና በተሰጣቸው ግምት ቤት እንዲስሩ ይደረጋል“።

አንተ የምትለው ለነበራቸው አሮጌ ቤት የሚሰጣቸው ግምት አዲስ ቤት ይሰራላቸዋል ነው?አልኩት

አዲስ ቤት ላይሰራላቸው ይችላል ። ግን ቆርቆሮም ገዝተው አጥረው መኖር ይችላሉ።

እንደ ሳውዝ አፍሪካ ታውን ሽፕ ዓይነት።

“ሌላ አማራጭ የለም። ሀገር ከዚህ ውጭ ልታድግ አይቻልም“ አለኝ።

ሕዝቡ ይህንን አይቃወምም እንዴ አልኩት።

“ሕዝብ ምን አቅም አለውና ነው ደግሞ እንደዚህ አይነት ጥያቄ የሚጠይቀው።ሕዝብን እንወክላለን የሚሉ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች እንኳ ይህንን ነገር አንስተው አልተቃወሙም።ተቃዋሚዎቹ እንዲያውም ለሃገሪቱ እድገት ነጻ ገበያ መፍትሄ ነው ሲሉ ነው የምንሰማው። ብዙዎቹ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ከመንግስት ጋር በሚሰሩበት ወቅት ኢንቨስተሮች የነበሩ ናቸው። አሁን ታቃዋሚዎች የሚባሉት እኮ የወያኔ አባላት የነበሩም ጭምር ናቸው።በሙስና ተወንጅለው ታስረው የተፈቱ፣ ስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አላግባብ ያካበቱ፣ በዘር ፖለቲካም ቢሆን ከሁሉም በላይ የነበሩ ናቸው። ወንድም አለም ይህ ሥርዓት በቅርብ ጊዜ ይጠፋል ብለህ አታስብ“።አለኝ

እዚህ እንደተሰማው ወያኔ በግንቦቱ ምርጫ የአዲስ አበባን ሕዝብ ስለተቀየመ ሕዝቡን ለማበሳጨት ሲል ሕዝቡ ከሚኖርበት ለማፈናቀል ነው ይህንን የጀመረው ነው የሚባለው።ብዬ ነገርኩት።

“ሀገር ቤት ብዙ ይወራል። ትክክል ሊሆንም ላይሆን ይችላል። እኔ ከቢዝነሱ ሰፈር ስለነበርኩ ታች ምን እንደሚወራ አላውቅም። እኔም እዚህ መጥቼ ነው ይህንን የሰማሁት። እነደነገርኩህ እናትና አባቴ ቤት አደለም  ያረፍኩት ። ሆቴል ይዤ ነው የከረምኩት። ታውቃለህ እናትና አባታችን ቤት ሽንት ቤቱም ፣መታጠቢውም አይመችም። ቤተሰቦቼ አንድ ሁለቴ ያለሁበት መጥተው ጠይቀውኛል። በቢዝነሱ ላይ ስራወጥ ግዜም አላገኘሁም። ለዚህ ይሆናል ያልሰማሁት“ አለኝ።

ግለሰቡ የት ሰንብቶ እንደመጣ ስለገባኝ እሺ ሃብቱን እንተውና የዘር ፖለቲካው ያልከውን አስረዳኝ ብዬ ጠየቅሁት።

„በጣም አታስቀኝ ከወያኔ ይብስ በዘር የሚያምኑ የተሰገሰጉት በተቃዋሚ ውስጥ መስሎኝ። ልጥራልህ እንዴ? ሃረጋዊ በርሄ ፣ ስዬ አብርሃ ፣ መረራ ጉዲና ፣ በየነ ጴጥሮስ ፣ ገብሩ አስራት፣ ሌንጮ ለታ እነዚህ ሁሉ በተቃዋሚ ውስጥ ሆነው በዘር ድርጅት የተደራጁ ናቸው። እንዲያውም ነጋሳ ጊዳዶ ፣ የኦሮሞ ፌደራሊስቱን ላንተ ብዬ አውጥቼልህ ነው። ከድርጅት ደግሞ ልንገርህ፣አራና ፣ የኦሮሞ ነጻ አውጭ ፣ የኦጋዴን ነፃ አውጭ፣የደቡብ ሕዝብ፣አብኮ፣ወዘተ ስንቱን ልጥቀስልህ የሚቀጥለውም መንግስትም ሊመሰረት የሚችለው በዘር ላይ ነው።ወንድሜ ጅል አትሁን። ያለቀለት የደቀቀለት ጉዳይ ነው።

ሌሎች ሕብረ ብሔር የሆኑ ድርጅቶች አሉ አደለም እንዴ? ብዬ ጠየቅሁት።

ጉድ እኮ ነው ሕብረ ብሔር ያልሆኑት ተቃዋሚዎች ሕብረ ብሔር የሆኑትን ተቃዋሚዎች ለማጥፋት እየታገሉ መሆናቸውን አታውቅም እንዴ? ብሎ አለኝ።

ይመስልሃል ወይ የሚያጠፉቸው? አልኩት።

"እሱ የእግዜር ጉዳይ ነው።በነፃ ገብያ ኢኮኖሚ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ ላይ አሸናፊ የሚሆነው መገለባበጥን የሚያውቅ ነው። ለአላማ መሞት ጥንት አክትሞል።መፈክሩ ትርፉ የሚያወጣ ከሆነ እናት ሀገርህንም መሸጥ ነው። የ 50 cents መፈክር "Get rich or die trying" የሚለውን አልሰማህም።ለምሳሌ ኢሕአፓን እንውሰድ እንውስድና እራሳቸው ተከፋፍለው አንዱ ክፍል ከወያኔ ጋር ለመግባት የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም ተብሎ አደለም እንዴ ሃገር ቤት የሚወራው"።

ይህም ይወራል እዛ ነው የምትለኝ?ብዬ ጠየቅሁት።

"ምንም የሚደበቅ ነገር የለም።ውጭ አገር የተሰራው ሁሉ አገር ቤትም ይወራል። ዋናው አሁን ልምከርህ ከፓለቲካ ድርጅት ገብተህ ከመዘፈቅ የሚዋጣህ ሃገር ወዳድ መሆን ነው። ሁላችንም ሃገራችንን እንወዳለን። እንዲያውም ማርና ወተትዋን የምትሰጠን ልጆቿ ደግሞ የበለጠ እንወዳታለን። ሃገር ወዳድ መሆን ሁሉን ነገር ይፈቅድልሃል።ስትፈልግ ትቃወማለህ ፣ ስትፈልግ ትደግፋለህ ፣ ስትፈልግ አስተማሪ ትሆናለህ ፣ ስትፈልግ ሠራተኛ ማህበር ትገባለህ ፣ ከቻልክም ሴቶች ማህበርም መግባት ትችላለህ። ቀኑ ሲሞላ ደግሞ ሁሉንም ሰድበህ ከመንግስት ተፋቅረህ ኢንቬስትር ትሆናለህ።ለምን ይመስልሃል ይህ ሁሉ ምሁራን ድርጅት ውስጥ የማይገቡት። ሃገር ወዳድነት ስለሚሻላቸው ነው። በፈለጉ ግዜ አቋማቸው ይቀይራሉ"።

አሁን ኢንቨስተር ሁን ስትለኝ ነበር። እንደገና ቀይረህ ደግሞ ሀገር ወዳድ ሁን ትለኛለህ። ምን ማለትህ ነው?

"አሁን በቀጥታ ኢንቬስተር መሆን አትችልም።ከመንግስት ጋር ተቋስለሃል። መጀመሪያ ኢትዮጵያውነትን አክራሪ ከሆኑ እንደነ ኢሕአፓ ፣ መኢአድ መራቅ አለብህ።እነዚህን አክራሪ ብለህ መሳደብ አስፈላጊ ነው ።አክራሪ የሚለው ቃል ከወያኔ ጋር ለመስራትም ቢሆን ፈቃደኛ እንደሆንክ ያሳያል።ከዛም ሀገር ወዳድ ሆነህ እራስህን ማስተዋወቅ ያሻል።ከዛ በኋላ ወደ ሀገር ቤት ሂደህ ሁኔታውን አይተህ ትመለስና በሚቀጥለው ጉዞህ በደንብ ተዘጋጅተህ ሂደህ ኢንቬስተር ትሆናለህ።ከዛም ፓራላማ ብትወዳደርና ብታሸንፍ እራስህን ብቻ ሳይሆን እኛንም ትጠቅማለህ" ብሎ ከልቡ ሳቀ።

ለመሆኑ ይህ ምክርህ እኔን ብቻ ነው ወይስ ሌሎችንም ትመክራለህ?

በተቻለኝ ሁሉንም እመክራከሁ። ለሰው ደግ ማስብ ጥሩ ነው ።መንግስትም ቢሆን ይህንን ጥረቴን ይመለከትልኛል።ዛሬ የመጣሁት እንኳ ጨዋታ ይዘን እረሳሁት እንጂ እዚህ ያለን ተሰብስበን መሬት እንዲሰጠን ልንጠይቅ ነውና የምትፈልግ ከሆነ እንድትመዘገብነው" አለኝ።

በል ይቅናህ እኔን እለፈኝ ብየው ተለያየን።

*ዛሬ ሃገራችን በእንደነዚህ ዓይነት ግለሰቦች ተሞልታለች።ከግል ጥቅማቸው ባሻገር ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ የማያስቡ አጋሰሶች በፖለቲካ ውስጥም አሉበት። ስንዴውን ከእንክርዳዱ መለየት ግን በጣም አስፈላጊ ነው። በወያኔ መድረክ ላይ ሊቀ መኳስ የነበሩ አሁን ደግሞ የተቃዋሚውን ጎራ እንምራው የሚሉ በዝተዋል። የተቃዋሚ ጎራም ውስጥ የነበሩ አንጃዎችና ባንዳዎች እነዚህ የቀድሞ የወያኔ አባላት ከወያኔ ያስታርቁናል በማለት ከሁሉም ጋር መስራት በሚል መፈክር ሃገራችንን ወደ በለጠ አዘቅት ውስጥ ለመክተት ጥረት ላይ ናቸው። ከሁላችንም የሚጠበቀው የአንድነት ሃይሉን አጠናክረን ወያኔንና የዘር ፖለቲካን ለአንዴም ለሁሌም ከአገራችን እንዲጠፉ ያላሰለሰ ትግል ማድረግ ነው።*

*በዚህ ዓይነት የወያኔ ሴራ የተጠመዱ ያሳዝኑኛል።ሰው ለሆዱ ሲያድርና ስብዕናው ሲያዋርድ ፣እድሜያችን ገፍቷል ብለው ለብዙ ዘመናት የቆሙለትን ዓላማ ሸጠው  የግል ጥቅማቸው የሚያሳድዱ ፣ በገሃነም እሳት ማህል ለሚፈጠር መንግስተ ሰማያት ሲሉ የሚራወጡ ያሳዝኑኛል።*

*በሌላ በኩል ደግሞ  ከሁሉ በላይ ግን ከቤቱ የሚፈናቀለው ሕዝብ ያሳዝነኛል።የሚበላው አጥቶ የሚሰቃየው ሕዝብ ያሳዝነኛል።በበሽታ ካለ እርዳታ የሚስቃየው ህዝብ ያሳዝነኛል። ሃገርህ አድጋለች እየተባለ የሚላገጥበት ሕዝብ ያሳዝነኛል።*

*ታላቁ የብዕር ሰው ደበበ ሰይፉ ለእራስ የተፃፈ ደብዳቤ በሚለው ግጥሙ በመጨረሻው አካባቢ እንዲህ ብሎ ነበር።*

*እና እዚያው እርስ በርሳችሁ ብትመሳጠሩ፣*
*ዕፁብ ድንቅ ተዓምር  ብትለፍፉ*
*ተረት ተረታችሁን ብታወጉ፣*
*በኔነት ማራቶን ብትዳፉ*
*በቋንቋ ስለት ብትዋጉ፣ለክብር ለስም፣ ብትዳሙ ብትጋፉ*
*በአለሁ ባይነት ብትፏድዱ ብትጣፉ፣.....*
*በዚህ ሙት ሕዝብ ፣በድክመቱ ብትልቁ፣*
*በፈተናው ብትበልጡ*
*በሱ ውድቀት እናንተ እርካብ ብትረግጡ*
*በብሶቱ ብትፈይዱ*
*በመከሊቱ ብትነግዱ ፣*
*ይህ ፍፁም ባድማ ፣ይህ ፍፁም ድቅድቅ ጨለማ*
*እሚበራ እንዳይመስላችሁ በናንተ የይስሙላ ቁራጭ ሻማ።*
*ግን መጋረጃው ያልተነሳ ተውኔት ያልተፈታ*
*እንቆቅልሽ አለውና ጨለማ*
*ነፋስ - እሳተ ገሞራን ፣ሊታቀፍ ይችላልና ጠፍ ባድማ*

*ዐይን ያለው ይይ !*
*ልብ ያለው ያስተውል!*
*ጆሮ ያለው ይስማ !*

*ስለተጨቆነ ሕዝብ የሚስብ በሰላም ይክረም።*

*በልጅግ አሊ የካቲት 2001*